
ዐውደ ጲላጦስ


ተስህቦ በኀብል


አክሊለ ሦክ


ተከርዖተ ርእስ


ተዐርቆተ ልብስ

# ፍኖተ መስቀል

*በሻምበል ጥላሁን*

ፍኖተ መስቀል ማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጲላጦስ ዐደባባይ አንሥቶ መስቀሉን ተሸክሞ እስከተሰቀለበት ተራራ እስከ ቀራንዮ ድረስ የተጓዘበት መንገድ ማለት ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሙስ ማታ እንደተያዘ ሌሊቱን ሁሉ መከራ ሲቀበል አድሮ ዓርብ ጧት የአይሁድ ሽማግሌዎችና አለቆች ተሰብሰበው ወደ ሹሙ ወደ ጲላጦስ ቤት ይዘውት ሔዱ፡፡ ከዚያም «ይህ ሰው ከሕጋችን ጋር የማይስማማ ትምህርት ሕዝቡን ያስተምራልና እንደ ሕጋችን ሞት ይገባዋል፡፡ ንጉሥ ነኝ፣ እያለም ያታልላል» በማለት በሹሙ ፊት ቀርበው ከሰሱት፡፡ ጲላጦስ ግን ብዙ ቢዋሹብትና ቢከሱት አላመናቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም መርምሮ በደል አላገኘበትምና ሊያድነው አስቦ ነበር፡፡ ግን ሊያድነው አልተቻለውም፡፡

ጲላጦስ ጌታችንን ሲመረምር ለብቻው አቁሞ መጠየቅ የሮማውያን ልማድ ነበርና አዳራሽ አስገብቶ ለብቻው የተከሰሰበትን ነገር ጠየቀው፡፡ አይሁድ ግን በዚህ ጊዜ በዓለ ፋሲካ ደርሶባቸው ነበረና ስለ በዓሉ ክብር ሲሉ ወደ ፍርድ ቤት አልገቡም፡፡ ከውጪ ተሰብስበው እርስ በእርሳቸው እንደፈቃዳቸውና እንደምኞታቸው ጌታን ለመስቀል ያስቡ ነበር፡፡ ጲላጦስም ጌታን ለብቻው በጥያቄ ከመረመረው በኋላ ከአዳራሹ ወደ ውጭ ብቅ ብሎ፤ በዚህ ሰው ለሞት የሚያበቃ በደል ወይም ምክንያት አላገኘሁብትም ያውላችሁ አላቸው፡፡ እነሱም «እንደ ሕጋችን ሞት የሚገባው ሰው ነው፡፡ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሏልና ሞት ይገባዋል፡፡ ስቀለው፣ ስቀለው» እያሉ መለሱለት፡፡ እሱም እንደገና ለብቻው ጠይቆና መርምሮ የሚሞትበት በደል እንደሌለበት ከዚያ በኋላ ከአዳራሹ ወደ ውጭ ወጣና ውኃ አስመጥቶ በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ፡፡ ከዚህም ሰው ደም ንጹሕ ነኝ ሞት አልፈርድበትም እያለ ሐቁን መሰከረ፡፡

አይሁድ ግን ይህ ሰው ንጉሥ ሳይሆን ንጉሥ ነኝ ብሏል፤ ንጉሥ ነኝ የሚል ሁሉ የቄሳር ተቃዋሚ ጠላት ነው፡፡ የቄሳር ወደረኛ መሆኑን እኛ እየመሰከርን አንተ ግን የቄሳር ሹም ሆነህ ብትለቀው አንተ ታውቀለህ እያሉ ጲላጦስን አስፈራርተውታል፡፡ ጲላጦስም ይህን ሲሰማ በራሱ ላይ ክስ እንዳይመጣበት ጌታችንን አሳልፎ ሰጧቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ጌታችንን ወታደሮቹ ተቀብለው ወደ ሌላ አዳራሽ አግብተው፤ ልብሱን ገፍፈው፣ ሌላ ቀይ ልብስ አልብሰው፣ የሾህ አክሊል በራሱ ላይ ደፍተው፣ ዘንግ በእጁ አስይዘው፣ ሎቱ ስብሐት «ንጉሥ ከሆንህ ለአንተ ስግደት ይገባል፡፡ ልብሰ መንግሥት ያምርብህ ይሆን? ክርስቶስ ከሆንህ ትንቢት ንገረን?» እያሉ፤ ፊቱን ሸፍነው ራስ ራሱን በዘንግ እየመቱ ከተሳለቁበት በኋላ ያለበሱትን ልብስ ገፍፈው የቀድሞ ልብሱን አልብሰው፣ መስቀሉን አሸክመው ወደ ሚሰቀልበት ቦታ ወደ ቀራንዮ ሲወስዱት የተነሡባት ቦታ ገበታ /ገበጣ/ ተብሎ ይጠራል፡፡

ከዚህ ቦታ /ከጲላጦስ ዐደባባይ/ ተነሥቶ መስቀሉን ተሸክሞ መከራውን ታግሶ እስከ ቀራንዮ የተጓዘበት ፍኖተ መስቀል ይባላል፡፡ ላቲኖች ጌታ በጲላጦስ ፊት ከቆመበት ቦታ ጀምሮ እስከ መካነ ትንሣኤው ድረስ በዕለተ ዓርብ የሆነውን ሁሉ እያነበቡና እየተረኩ ወደ ላይ ወደ ቀራንዮ ይገባሉ፡፡ በየጉዞው ላይ ጸሎት የሚያደርጉባቸው ፲፭ ምዕራፎች አሉ፡፡

## የፍኖተ መስቀል ምዕራፍ የጲላጦስ አደባባይ /ገበታ/

የመጀመሪያው ምዕራፍ ጌታ ከጲላጦስ ፊት ለፍርድ የቆመበት ዐደባባይ ነው፡፡

ስሙም በዕብራይስጥ ገበታ፣ በግሪክ ሊቶስጥራ ይባላል፡፡

## ጌታ የተገረፈበት

ሁለተኛው ምዕራፍ ከሊቶስጥራ ወጥቶ ወደ ጌቴሴማኒ የሚወስደውን መንገድ ተሻግሮ ጲላጦስ ጌታን ገርፎ ያ ሰው ያውላችሁ ያለበት ነው፡፡ የቦታው ስም እስከ ዛሬ ጌታ የተገረፈበት ይባላል፡፡ በቦታው ላቲኖች ገዳም ሠርተውበታል፡፡

## ጌታ በመጀመሪያ የወደቀበት ቦታ

ሦስተኛው ምዕራፍ፤ የቀደመውን ሥፍራ ወደኋላ ትቶ ወደ ምዕራብ የሚወስደውን መንገድ ይዞ በደማስቆ በር መግቢያ የአርመን ቤተክርስቲያን ያለበት በሩ በብረት የታጠረ ትንሽ ክፍል ነው፡፡ ጌታ ከዚህ ሲደርስ ከግርፋቱ ጽናት እና ከመስቀሉ ክብደት የተነሣ የወደቀበት ነው፡፡ ስለዚህ ቦታው ጌታ በመጀመሪያ የወደቀበት ይባላል፡፡

## እመቤታችን እያለቀሰች ልጇን ያገኘችበት ቦታ

አራተኛው ምዕራፍ፤ ከሦስተኛው ምዕራፍ ትንሽ ዝቅ ብሎ ከአርመን ገዳም በስተግራ ካለው ማዓዝን ሲደርሱ እናቱ ድንግል ማርያም እያለቀሰች ከልጅዋ ጋር የተገናኘበት ቦታ ነው፡፡

## ቀሬናዊ ስምዖን የጌታን መስቀል የተሸከመበት ቦታ

አምስተኛ ምዕራፍ፤ ከአራተኛው ሃያ ሜትር ያህል ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከተጓዙ በኋላ ወደቀኝ የሚታጠፈው መንገድ ነው፡፡ በዚህ ቦታ ላይ ስምዖን ቀሬናዊ የሚባል ሰው ከእርሻው ውሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ ወታደሮች አግኝተውት አስገድደው እየጎተቱ ወስደው የጌታን መስቀል ያሸከሙብት ቦታ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ተግባር በወታደሮቹ ዘንድ የተለመደ ነበረና፤ በዚህ ቦታ ላቲኖች ትንሽ መቅደስ ሠርተውበታል የስምዖን መቅድስ ይባላል፡፡

ይህ ስምዖን የተባለው ሰው የእስክንድሮስና የሩፎን አባት ነው፡፡ ማር. ፲፭÷፳፩፡፡ ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ ፲፮÷፲፫ በሰላምታው ውስጥ ሩፎን ያነሣዋል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ልጆቹ ቁጥራቸው ከ፸፪ አርድእት ነው፡፡ ይህም ሰው ምንም እንኳን ተገድዶ ቢሆንም የጌታን መስቀል በመሸከሙ የበረከተ መስቀሉ ተሳታፊ ሆኗል፡፡ ስለ ሆነም ዕደለኛ ሰው ነው፡፡

## ቬሮና /ስራጽታ/ በመሐረብ የጌታን ፊት የጠረገችበት ቦታ

ስድስተኛው ምዕራፍ፤ ቬሮና /ስራጽታ/ የምትባል ሴት ከግርፋቱ ጽናት፤ ከመስቀሉ ክብደት የተነሣ፤ ፊቱን የደምወዝ አልብሶት ስታየው አዝና ፊቱን በነጭ መሐረብ ስትጠርግለት ወዲያውኑ አምላክነቱን የሚገልጥ፣ ለበጎ ሥራዋም ተስፋ የሚሰጥ፣ ሃይማኖቷን የሚያበረታታ የፊቱ መልክ በመሐረቡ ላይ ተገኘ፡፡ እሷም በዚህ ምክንያት እምነቷ እጅግ የጸና ሆነ፡፡

ታሪኳን ወይም በጎ ሥራዋን የሚናገር ወንጌላውያን በጻፉት ወንጌል አይገኝም፡፡ ነገር ግን ታሪኳን የተለያዩ የቤተክርስቲያናችን መጻሕፍት ይናገሩላታል፡፡ አንዳንድ አባቶችም ስለዚች ሴት ሲናገሩ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ደም ሲፈሳት ቆይታ የጌታን ልብስ ጫፍ በመዳሰሷ የዳነችው ሴት ናት ይላሉ፡፡ በዚህ በስድስተኛው ምዕራፍ ላይ ግሪኮች መቅደስ ሠርተውበታል፤ ዓርብ ዓርብ በየሳምንቱ ይከፈታል፡፡

## የጎልጎታ መቃረቢያ

ሰባተኛ ምዕራፍ፤ ከስድስተኛው በግምት አንደ መቶ ሜትር ያህል ተጉዞ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በሚወስደው መንገድ ከሰሜን አቅጣጫ መጥቶ ወደ ጽርሐ ጽዮን በሚያሳልፈው መካከለኛ መንገድ ላይ ነው፡፡ በጌታችን ዘመን የከተማው መጨረሻ የምዕራቡ በር ይህ ነበር ይባላል፡፡ በዚህም ቦታ ትንሽ መቅደስ አለበት፡፡ በውስጡ በቀድሞ ዘመን የነበሩ አዕማድ ናቸው እያሉ ያሳያሉ፡፡ መቅደሱ የላቲኖች ነው፡፡ እንደ ታሪኩ ቦታው ጥንት የከተማው በር ነበረ ይባላል፤ እንደ ዚህ ከሆነ ጎልጎታ ከከተማው በጣም ሩቅ አልነበረም፡፡

## የጌታችንን ሥቃይ ሴቶች አይተው ያለቀሱበት ቦታ

ስምንተኛው ምዕራፍ፤ ከሰባተኛው በአሥራ አምስት ሜትር ያህል ወደ ላይ ወጣ ብሎ ይገኛል፡፡ ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ መከራ መስቀልን እየተቀበለ ሲሔድ ሴቶች አይተው እያለቀሱ ሲከተሉት ወደነሱ መለስ ብሎ፤ እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች ለኔ ማልቀሳችሁ ቀርቶ ለራሳችሁ አልቅሱ ያለበት ቦታ ነው፡፡ ሉቃ.፳፫÷፳፯፡፡ ጌታ ይህን ማለቱ ከአርባ ዘመን በኋላ የሚመጣባቸውን መከራ በትንቢት ሲነግራቸው ነው፡፡ በዚህ ቦታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሆኑ የመነኮሳት መኖሪያ አራት ቤቶች አሉ፡፡

## መስቀል ይዞ የወደቀበት

ዘጠነኛ ምዕራፍ አንድ የቆመ የድንጋይ ዓምድ አለበት፡፡ በዚህ ቦታ ጌታ መስቀል ይዞ ወድቆበታል፡፡ ይህ ቦታ ወደ ጎልጎታ መውጪያ በር ነው፡፡ ቦታው የኢትዮጵያ ገዳማት መግቢያ በር ነው፡፡

## ልብሱን የገፈፉበት

አስረኛው ምዕራፍ፤ የጌታን ልብስ የገፈፉበት ቦታ ነው፡፡

## ጌታን የቸነከሩበት

አስራ አንደኛው ምዕራፍ ጌታን ልብሱን ገፍፈው ዕርቃኑን ካስቀሩት በኋላ እጆቹንና እግሮቹን በምስማር የቸነከሩበት ቦታ ነው፡፡

## መስቀሉን ያቆሙበት ቦታ

አስራ ሁለተኛው ምዕራፍ ጌታን በመስቀል ላይ ከቸነከሩት በኋላ መስቀሉን ያቆሙበት ቦታ ነው፡፡

## ቅዱስ ሥጋውን ያወረዱበት ቦታ

አስራ ሦስተኛ ምዕራፍ እነ ኒቆዲሞስ ጌታን ከመስቀል ያወረዱበት እና ያሳረፉበት ቦታ ነው፡፡

## ቅዱስ ሥጋውን የገነዙበት ቦታ

አስራ አራተኛው ምዕራፍ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የጌታን ቅዱስ ሥጋ የገነዙበት ቦታ ነው፡፡

## ቅዱስ ሥጋው የተቀበረበት ቦታ

አስራ አምስተኛው ምዕራፍ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የጌታን ቅዱስ ሥጋውን በአዲስ መቃብር ያሳረፉበት ቦታ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፍኖተ መስቀል ምዕራፎች እነዚህን ናቸው፡፡ ✞

*ምንጭ- ታሪክ ነጋሪ የመንገድ መሪ፤ መጽሐፍ አዘጋጅ መጋቢ አባ ፍስሐ ጽዮን በየነ ፳፻፩ዓ.ም፤ ሜጋ ማተሚያ*

ተቀስፎ ዘባን


ስቅለት


አውረድዎ እምዕፅ


ገነዝዎ በሰንዱናት


ቀበርዎ ውስተመቃብር ሐዲስ
